# ሄንሪ ግሩቨር - በጸሎት የእግር ተጓዥ

## ኦክቶበር፣ ኖቬምበር 2012 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ጃፓን የተልዕኮ ጉዞ

ሄንሪ ግሩቨር፥ በሀገራት እየተዘዋወሩ በተለያዩ ጎዳናዎች ላይ ስለዛች ምድር፥ ቦታ፣ ሰፈር፣ አካበቢ ወዘተ በእግራቸው ለረዥም ሰዓታት እየተመላለሱ የሚጸልዩና የሚማልዱ እንዲሁም ሀገራትን በጸሎት ለክርስቶስ ኢየሱስ የሚማርኩ ሰው ናቸው።

በዚህ መኸር የጃፓን ጉዞዬን ከብዙ የረዥም ሰዓታት ተከታታይ በረራዎችና እረፍቶች (connecting flights and layovers) በኋላ በቶኪዮ ናሪታ አየር ማረፊያ በመድረስ ጀመርሁ። ናሪታ አለማቀፍ የአየር ማረፊያ ደርሼ መፈጸም የሚገቡኝን ከፈጸምሁ በኋላ በዓለም አቀፍ (የወንጌል) ስርጭት ተልዕኮ ማእከሉ አስተርጓሚዬን ለመገናኘት በባቡር ወደ ኢዋኪ ከተማ ሄድሁ። (Narita Int'l Airport, Iwaki City Japan፣ Global Mission Outreach Center)

በመጀመሪያው ምሽት በጣም በተቀባች አንዲት ጃፓናዊት ድምጻዊ በተዘጋጀ ዝግጅት (ኮንሰርት) ተደሰትሁ፡፡ ዘፈኖቿና በጃፓን ካሉ ታዋቂ እጅግ ዝነኛ ዘፋኞች መካከል አንዷ ወደ መሆን ያደረገችው ጉዞ ስላጋጠመው የማንኛውም ድምጻዊ የከፋው ፍርሀት ምስክርነቷ። በድንገት ድምጿን አጣች ማንምም የህክምና ባለሙያ ድምጿን መልሳ እንድታገኝ ሊረዳት አልቻለም። ከዚያም ደግሞ የ2007 ዓ.ም[፥] (እ.ኤ.አ) መሬት መንቀጥቀጥና ጎርፍ (ሱናሚ) ሆካኢዶ ደሴትን ሲመታና ብቸኛ ውድ ወንድሚን ሲወስድባት ሌላ አስከፊ ሁኔታ ደረሰባት። በአጥፊው ጉዞውም የልጅነት ቤታቸውንና እርሻቸውን ሙሉ በሙሉ አጥፍቶታል። ህይወቷ ወደ ፍፃሜው የመጣ ነው የሚመስለው። አሁን፥ ሥራዋ ብቻ አይደለም፥ የተረፋት ብቸኛ ቤተሰቧም ጠፍቷል። ይህ አብዛኞቹ ጃፓናዊያን ቤተሰቦች በማርች 11፣ 2010 የጃፓንኗን ሳንዳይ ግዛት የመታውን ባለ 9.2 መሬት መንቀጥቀጥ እርሱንም ተከትሎ በታሪክ አጅግ አስከፊ ከሆኑት አንዱ በሆነው በባሕር ማዕበል መጥለቅለቅ (ሱናሚ) ወደ ደረሰባቸው ስፍራ (ሁኔታ) አመጣት። ከ100 ጫማ (ከ30 ሜትር በላይ) በላይ ከፍታ ያለው ከባሕር በታች በተከሰተ የመሬት መንቀጥቀጥ እየጨመረ በሚሄድ የባሕር ማዕበል በሰላማዊ ውቅያኖስ (ፓስፊክ ኦሽን) ጠረፍ ታንሺ ደሴትን ጨምሮ እስከ 250 ማይልስ (ከ400 ኪ.ሜ. በላይ) እርቀት ድረስ በመንገዱ ያገኘውን ሁሉ እያጠፋ ሲጓዝ። የሚኞች ቁጥር እስካሁን አልታወቀም ምክንያቱም ብዙ ቤተሰቦች በመንግሥት ቢሮዎች ከነበሩ መዝገቦቻቸው ጋር አብረው ጠፍተዋል። ሁሉም በውኃና በእሳት ተጠርገው ተወስደዋል ወድመዋል። ከዚያ ደግሞ በሩሲያ ቼርኖቤል እንደተከሰተው እስካሁንም ከተማዋን የሙት መንፈስ መንደር (የወደመች ከተማ) አደርጎ እንዳስቀራት የኒውክሊየር መቅለጥ አደጋ ፉኩሺማ ግዛትን ከገዳይ ጨረር ጋር የተዋት፥ የዲኤቺ ኒውክሊየር ማብላያ ፍንዳታ። (Honshu Islands Pacific Coast፣ Diaechi Necular Power Plant፣ Fukushima prefiction (or state)፣ Russia's chernoble melt down፣ ghost town area)

ከዚያም በዚህች ወጣት ድምጻዊ ህይወት ውስጥ አስደናቂ ነገር ተፈጠረ። በጭንቅ ወደ ቡዳህ ከጮኸች በኋላ ስለኢየሱስ ፍቅርና የእርሱን አስደናቂ ጸጋ የነገረቻትን አንድ ክርስቲያን አገኘች። ይህን ሀሳብ ከአዕምሮዋ ልታወጣው አልቻለችም ከዚያም ወደ ኢየሱስ ለእርዳታ ጮኸች። መላ ማንነቷን ፈጽሞ አጋጥሚትና አይታው የማታውቀው ሀሴትና ሰላም ሲሞላት አስደናቂ መለወጥን ተለማመደች። ቤተክርስቲያንም ፈለገችና የተራበች ሰባራ ነፍሷን የመገባት መጽሐፍ ቅዱስ አገኘች። አንድ ቀን ለመዝፈን ጥልቅ የሆነ ፍላጎት ሲያድርባት በዚህ ጊዜ ስለኢየሱስ ነው፣ ድምጿ እንደቀድሞው የሚያምር ሆኖ ተመለሰላት። አሁን ትዘምራለች ታሪኳንም ትናገራለች ለውድ አዳኟ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ። በሺዎች ለሚቆጠሩ ከአደጋው ለተረፉ ሰዎች የጃፓን መንግሥት በሰጠው ተሳቢ በሚመስሉ መጠለያዎች በሚኖሩበት የአደጋው መስመር አካባቢ ሙሉ ጊዜዋን ለዚያ ሰጥታለች።

የምሽቱ ዝግጅት (ኮንሰርት) ለእኔ ደስ የሚል የንጹህ አየር ትንፋሽ ነበር። ቤተሰብ ጓደኞችና ያላቸውን ንብረቶች ካጡት ሰዎች ጋር በዚያ ተቀምጬ፥ የ36 ሰዓታት ጉዞዬ ከድካም ወደ ብርታት ታድሶ ለ5 ሳምንታት አገልግሎት ለጃፓን ሕዝቦች በአዲስ ፍቅርና ቅናት ዝግጁ ሆንሁ።

አዳሬን ጥሩ እንቅልፍ ከተኛሁ በኋላ ከተወደደው ወንድሜና አስተርጓሚዬ አኪራ ሞሪ ጋር በመኪና ጉዟችንን ጀመርን። አኪራ በጣም ጎበዝ ሹፌር ነው ጂ.ፒ.ኤሱንና ኤይፎኑን በመጠቀም ልዩ ችሎታና ታላቅ ጸጋ አለው፥ በዚህም በደሴቱ ውስጥ በጥሩ ስኬት አለፍን። (GPS, I-Phone)

የመጀመሪያ ቀናችን በሆንሹ በሰላማዊ ውቅያኖስ በኩል ከምትገኘው "ኢዋኪ" በባሕሩ በጃፓን በኩል ወደምትገኘው "ኦዴት" ከተማ ነበር፥ በዚያም ያሉትን ሰዎች እንደገና ላያቸው ጓጉቼ ነበር። በዚያ አካበቢ የ4 ዓመት የመንገድ ላይ (እየሄዱ ጸሎት) ጸሎት ከጨረስን 6 ዓመት ሆኖታል። ከ6 ዓመታት በፊት ቤተክርስቲያኑ መጋቢውንና (ፓስተሩን) ባለቤቱን እንዲሁም 3 ልጆቻቸውን ጨምሮ 20 አባላት (ምእመናን) ነበሩት። ወጣት ቤተሰቦች ነበሩ ይህም ለቦታው ቀዳሚውና የመጀመሪያ ቤተክርስቲያናቸው ነበር። በጃፓን ቶኪዮ ውስጥ በሚገኝ "ሜዶ ሪኖ ማኪባ" የሚባል ትልቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልግሎት ተሾመው ነበር በጃፓንኛ ትርጉሙ "የአረንጓዴው ሸለቆ ቤተክርስቲያን" ማለት ነው። ("Iwaki"፣ Honshu፣ City of "Odate"፣ "Medo Rino Makiba" meaning in Japanese- Church of the Green Valley.")

ከስድስት ዓመታት በፊት የነበረኝ የኦዴት ከተማና አካባቢዋ ትውስታ የጭንቀት (የተከፋች) ከተማና አዛውንቶቻቸውን አስገብተው የሚሰናበቱባቸውና፥ እዛው እንዲሞቱ የሚተዉበት ዝነኛ ዋሻዎች ያሉባት እንደነበረች ነው። በእነዚህ ዋሻዎችና ድህነት ግልጽ በሆነባቸው አካባቢዎች ላይ ጸልየናል። እንዲሁም በብዙ ጎዳናዎች ላይ በህይወት ለመቆየት (ለመኖር) የማያቋርጡ ትግሎችን እያስተዋልን ተመላልሰናል። በዚህ ዓመት ወደ ኦዴት ከገባሁ በኋላ፥ መላው አካባቢ ሙሉ በሙሉ ስለተቀየረ በጣም ተገርሜ ነበር። ቤቶች በብዙ አበቦችና በጤናማ አረንጓዴ ተክሎች በደንብም ከተጠበቁ የአትክልት ቦታዎች ጋር ተሻሽለዋል። ለአኪራ "*እርግጠኛ ነህ ይህ ኦዴት ነው?*" አልሁት። "*አዎ፥ ለምንድ ነው እንደዚህ የተደነቅሽው?*"" አለኝ። እኔም፡ "*ከስድስት ዓመታት በፊት በየዓመቱ የተመላለስንበት ሌላ ከተማ ሊኖር ይገባል ይሄ አዲስ ከተማ ነውና። በከተማዋም ያለው መንፈስ ቀለል ያለ ነው*" አልሁት። ከመጋቢውና ከባለቤቱ ጋር ከተገናኘን በኋላ ወደ አዲሱ ቤተክርስቲያን ሄድን። ትንሿ ቤተክርስቲያናቸው ከ100 ሰው በላይ የምታስቀምጥ የምታምር ቤተክርስቲያን ሆና አድጋለች። አሁን ያማረ መገልገያ ቦታ አላቸው እንዲሁም ደግሞ አሁን መረጃችሁን የምታድሱት አብራችሁ ለሰዓትት መንገድ ስትሄዱ ከነበሩት አዋቂዎች ብቻ አይደለም፥ በአስራዎቹ መጨረሻ እድሜያቸው ጥሩ ዘማሪዎች ከሆኑት ጋር፥ አሁን እንደ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ከእነርሱም ጋር መተዋወቃችሁ ሀሴትን ይሰጣል።

በ2006 ዓ.ም ስለሄድንበት አንድ ትንሽ አካባቢ መዘገብ እፈልጋለሁ። የተለያዩ ቡድኖች መከለያ የነበረች ትንሽ የከተማ መናፈሻ። የመናፈሻው አካባቢ በቆሻሻ የተሞላና፥ ከመከለያውም ጀርባ ብዙ ዓይነት አስጸያፊ ጽሑፎች ይገኛሉ፥ የተረበሹ ወጣት ልጆች ከእይታና ከቁጥጥር ውጪ በሚሰባሰቡባቸው ስፍራዎች የሚታይ ነው። በኦክቶበር 14፣ 2012 ዓ.ም ተመልሰን ወደ መናፈሻው ስንገባ ባየሁት ለውጥ ተባርኬያለሁ። አዲስ መጫወቻ ስፍራ፥ የሚያምር መልካምድር፥ የሲሚንቶ ንጣፍ መሄጃዎች፥ ረዥም ፏፏቴ አለው። መከለያውም እንደገና ተሠርቶ ምንም ጽሑፍም ሆነ ፊደል የለበትም። ሙሉ ለውጥ።

የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በበላይ ተቆጣጣሪው እየተመራን ብዙ አካባቢዎችን ጎበኘን። የአዕምሮና የአካል ችግር ላለባቸው ልጆች የተዘጋጁ ጥሩ አቅራቦቶችን ጨምሮ ብዙ አዳዲስ ሕንጻዎች ነበሯቸው። ጎበኘን በትምህርት ቤቱም ሙሉ ጸለይን። በከተማዋ እርዳታ የተሠራ አንድ ክፍል ደግሞ በተለየ የሚስብ ነበር። ከ1945 ጀምሮ የኦዴት ታሪክ ነበረ። በጽሑፍና በምስል ተገልጸው፤ በጉብኝቱ ውስጥ ወደ ኋላ የዘገየሁበት ያ ክፍል ነበር። በነዚያ በምስሎቹ ውስጥ አሮጌዋ ኦዴት ሳትለወጥ ከጦርነቱ ጊዜ አንስቶ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ አለች፥ ከዚያም ከ2005 ጀምሮ እስከ 2011 ዓ.ም በጣም ግልጽ የሆነ ለውጥ ይታያል። ሙሉ በሙሉ ልዩ ከተማ ነው የሚመስለው። እያንዳንዱ በ(ሰዎች) ፊቶች ላይና በመላ አካባቢዎች ላይ ያሉ ለውጦችን እያየሁ ስሄድ እንባዬን ወደ ኋላ እየታገልሁት ነበር።

እኛ የታሰሩትን ከፈታን፥ ከተማዋን (ከኃጢአት) ካጸዳን፥ እናም ፍቅርን፥ ተቀባይነትንና ይቅርታን ከበረከት ጋር ካወጅን፥ ያሑዋሕ በሕዝቡና በአካባቢው ማድረግ በሚችለው ነገር ልቤ በፍጹም ምስጋና ተሞልቶ ኦዴትን ተለየኋት።

ማርች 17 በመጋቢ አኪማሳ ሳሳኪ አስተባበሪነት በተዘጋጀ የሁሉም ጉባኤዎች መጋቢዎችንም ያሳተፈ አካባቢ አቀፍ ጉበኤ ላይ አኦሞሪ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ተሰባሰብን። መሰባሰባችን ደስ የሚልና ስለ "የእግር ጉዞ

ጸሎት” የበለጠ ለመማር ጉጉ የሆኑ ብዙ መጋቢዎች የተገኙበት ነበር። (Aomori Baptist Church፣ Pastor Akimasa Sasaki)

በሚቀጥለው ቀን ከ110 ዓመታት በፊት ጃፓን ከሩሲያ ጋር በነበራት የክረምት ጦርነት ወቅት ወታደሮችን ለማሰልጠን ያገለግል ለነበረ ቦታ ለመጸለይ ወደ ተራራ ወጣን። ያ ክረምት በዚያ ተራራ ላይ እጅግ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ሰው ስለተልዕኮው መረጃ ለማድረስ በሚመለስበትና እርዳታ ሰጪዎች በሚመጡበት ጊዜ ውስጥ 193 ሰዎች (በኒውክሊየር የአየር ብክለት) ተጋልጠው ሞቱ የተረፉ 17 ሰዎችን ማዳን ቢችሉም እነርሱም ብዙም ሳይቆዩ በረሀብ፥ በቅዝቃዜና፥ በመጋለጥ ሞቱ። የመጨረሻዎቹን 17 ሰዎች ወዳዳኑበት ቦታ በእግር ሄድን። ለተረፉት ቤተሰቦችና በዚያ ከፍተኛ ተራራ ላይ ስላለው የሞት ቃልኪዳን ለይቅርታና ለፈውስ ስንጸልይ ልባችን እጅግ ከብዶ ነበር።

እንዲሁም ደግሞ ስለ“አኦያጊ” አካባቢ፥ “ሀራኦካ አፐሮር” ስለሚባል ከአኦሞሪ ከተማ ወጣ ብሎ የሚገኝ ጎዳና ጸለይን። በጁን 4፣ 1947 ዓ.ም 170 ቻይናውያን ለ16 ሰዓታት የከሰል ማእድን ማውጫ ውስጥ በአግባቡ ሳይመገቡ የሚሠሩበት ከከፍተኛም የሥራ ጫና የተነሳ ሞቱ። አምጸውም ወደ ጫካው ሸሹ፥ ነገር ግን በ7 ወራት ተይዘው ለብዙ ቀንና ሌሊቶች ከዛፍ ጋር ታሰሩ። ብዙዎች ሞቱ ሥጋዎቻቸውም ምንም ክብር ሳይሰጣቸውና ያለምንም ቀብር በጉድጓድ ውስጥ ተጣሉ። ካመጹት 986 ቻይናውያን ሠራተኞች “አክመድ” ማለትም “የጋራ ደስታ ቤት” ተብሎ በሚጠራው ቤት ተጠልለው ከነበሩት መካከል አብዛኞቹ ከከባድ ሁኔታዎችና ከሀዘን የተነሳ ሞተዋል። የማስታወሻ ሐውልት (ድንጋይ) እነዚያን ቀናት እየዘገበ በዚያ ቆሟል። በእርግጥም ይህ ቦታ አሁን ድረስ በድህነት የተመታ ነው። ለመጋቢው አካባቢው በአሳሳቢ ሁኔታ ጸሎት እንደሚያስፈልገው ነገርሁትና እንደዛ ለማድረግ ተስማማ። መጋቢ አኪማሳ ሳሳኪ ተስማማና ሁላችንም በመታሰቢያ ሐውልቱ ዙሪያ ለመጸለይ እንደምንስማማ ጠየቀ። ድንጋዩ በዚህ የከሰል ማዕድን ስፍራ ሲሠሩና በአካባቢው ለመስኖና ጎርፍ መከላከያ ጉድጓድ ሲቆፍሩ የነበሩት የ986ቱ ቻይናውያን ስም ተጽፎበታል። ረዥም ጥቁር የሚኞቹ ስም የተዘረዘረበት ሐውልት ያለበት የተከለለ ስፍራ አገኘን። ከቻይና ማንቹሪያ በመጡ የሚኞች ዘሮች (ቤተሰቦች) የገንዘብ ድጋፍ የተሠራ ነው። በዓመት አንድ ጊዜም ቤተሰቦቻቸው እየመጡ ለሚኞቹ ክብር ይሰጣሉ። እንዲህ ዓይነቱ መታሰቢያ ከቻይና፥ ከኮሪያና ከፊሊፒንስ በመጡ ሰዎች በመላው ሆንሹ ደሴት ይደረጋል። ለዚያች ምድር ሰዎች እየመጡ አክብሮታቸውን መስጠት የተለመደ ነው። (“Aoyagi,”፣ Aomori፣ “Haraoka UpRoar”፣ “Akmed” or “House of Corporate Enjoyment”፣ Pastor Akimasa Sasaki፣ descendants of Manchuria China፣ China, Korea, and the Phillipines)

ወደ ጉድጓዱ ተመልሰን፥ ወደ አካባባዊ ስንደርስ፥ በጊዜው በዚያ ወደ ነበረ የቡድሀ አምልኮ ቤት ደረስን። አሁን በሀላፊነት ላይ ያለው ካህን በ1945ቱ ክስተት ጊዜ የነበረው ካህን ልጅ ነው። (budah temple)

በአምልኮ ቤቱ ዙሪያ እየዞርንና ኃጢአቶቹን እያስተሰረይን እንዲሁም ስለዚህ መተላለፍ **የከበረው ጌታችን** ስለከፈለው፥ ደሙን፥ ሥጋውን፥ አዕምሮንና መንፈስን እየወረሰን (እያወጅን)፥ ከዚያ ደግሞ እኔ አሁን በህይወት ላሉቱ በፊት በቤተሰቦቻቸው ጭቆና ስለደረሰባቸው ነጻነትን አወጅሁ። **ውዱ ጌታ** ፈውስንና በቻያና ማንቹሪያና በጃፓን መካከል ማስታረቅን እንዲያደርግ እየጠየቅሁኝ። ከዚያም **ለጌታ** የውዳሴን መዝሙር ዘመርን በሮሜ 8፡19-23፣ ኢሳይያስ 51፡1-3 ቃል መሠረት ፍጥረት ሁሉ ከእርግማን ነፃ እንዲሆኑ አወጅን። መጋቢው እኔ የቡድሀውን ካህን እንዳናግረው ፈልጎ ነበር። የላይኛውን እስክንጨርስ ድረስ **ክቡር ጌታችን** ከአምልኮው ቤቱ ማንም አልነበረውም፥ ነገር ግን ልክ እንደጨረስን፥ የቡድሀውን ካህን ከነሚስቱ ወደ ውጭ አወጣቸው። እንዴት ያለ ፍጹም የሰዓት መገጣጠም ነው፥ **ያሑዋሕ** ይመስገን። ተዋወቅንና ወደ መታሰቢያው ጉድጓድ ሊወስደን እንደሚፈልግ ነገረን። እኛም “*እሺ፥ ደስ ይለናል!*” አልነው።

ከመጀመሪያው ደቂቃ ጀምሮ ከአምልኮው ቦታው አካባቢ ወደ መታሰቢያው ጉድጓድ እየሄድን **የኢየሱስ ፍቅር** ከእኛ ውስጥ በኃይል ይሰማው እንደነበረ ግልጽ ነበር። ከተራራው አጠገብ ጀምሮ እስከቆምንበት አጠገብ እስከ ጉድጓዱ አሳየን። ወደ እኔ እየተመለከተ እንዲህ አለ፡ “*እዚያ ታች የሩዙ እርሻ ቦታ ነበር የአሜርካ ምርኮኞች ጦርነቱ እስኪያልቅ ድረስ ተጠብቀው የነበሩት፥ እናም ብዙ የአሜሪካ ወታደሮች በዚያ እንደታሰሩ ሞተዋል።*” ከዚያም ወደ ምልክቱ ፊቱን አዞረና፥ በአንድ በኩል ቆሞ የአባቱን የልብ ስብራት እንዴት በእየቀኑ እየመጡ ምንም ጥቅም እንደሌላቸው በጉድጓዱ ውስጥ ለሚጣሉት ሰዎች ክብሩን ለመግለጽ

እንደተከለከለ አስረዳን። አባቱ መልካምና አዛኝ ሰው እንደነበረና በዚያ አካባቢ ባሉ ሰዎች ዘንድ የተወደደ እንደነበረ ነገረን። እርሱ አሁን በዚያ በካህንነት ያለው ለዛ እንደሆነ ያምናል።

ከጨረሰ በኋላ፥ በዚያ አካባቢ ላይ መጸለይ እንደምፈልግ ጠየቀኝ። አዎ በጣም እንጂ አልሁት። እባካችሁ ጮኽ ብላችሁ ለመጸለይ ነፃነት ይሰማችሁ አለን። ልባችሁ በፈቀደው በማንኛውም ቃላት። ከዚያም በእርሱ ላይና በባለቤቱ ላይ ለመጸለይ በቃን። ብዙ እንባዎች ፈስሰው ነበር። ከእርሱ ጋር ከአምልኮ ቤቱ መውጫ ወደ በሩ ስንሄድ በጣም ልዩ የሆነ መገኘት ነበር። እጁን ጨበጥሁትና ፈገግታችንና ደስታችን ሁሉን ተናገረው። መጋቢው በልዩ ደስታና መበረታታት ተሞልቶ ነበር። በዚያ ምሽት መሰባሰባችን ላይ መግቢያው ላይ፥ የቀኑ የእግር ጉዞአችን እንዴት ድንቅ እንደነበረ ሲናገር ሲናገር ቆየ።

ይህ ክስተት በጃፓን ሀገር ስንራመድ አሁንም አሁንም ራሱን ደጋገመ። ያለፈውን የ5 ሳምንታት ጉዞዬን ዞር ብዬ ስመለከተው፥ በሜዳው፣ በተራራው፣ በወንዞቹ ሁሉ አቋርጠን ስንራመድ እንዲሁም ውቃቢዎች (shaman) የቀደሙት አባቶቻቸውን መናፍስት የሚጠሩባቸው ጨለማ ዋሻዎች ውስጥ ስናልፍ። (ያው የታወቀን መንፈስ (እርኩሳን መናፍስትን) ነው የሚጠሩት፥ እውነተኛውን ሰውዬ አይደለም።) ይህ ሁሉ ምን ፋይዳ አለው? ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ።

ይህን ልበል - የእኛን ዳና ተከተሉና እየሆኑ ያሉትን ብዙ ለውጦች ተመልከቱ። በመተማመን፥ በእምነት፥ በየቀኑ የእግር ጉዞ ጸሎት ቡድናችን ለሚያካፍለው ትምህርት ምላሽ በመስጠት ጌታ በየቀኑ እየሠራ ያለውን እየተመለከትን ጉዞአችንን ስንቀጥል፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለመጋቢዎችና ለሕዝባቸው እውነቱ ወጥቶላቸዋል።

ይህ በያሕዌሕ ቃል በጥሩ ሁኔታ ተግልጿል።

መዝሙር 90:12 በልብ ጥበብን እንድንማር፥ ቀኝህን እንዲህ አስታውቀን።
13 አቤቱ፥ ተመለስ፥ እስከ መቼስ ነው? ስለ ባሪያዎችህም ተምዋገት።
14 በማለዳ ምሕረትህን እንጠግባለን፤ በዘመናችን ሁሉ ደስ ይለናል ሐሤትም እናደርጋለን።
15 መከራ ባሳየኸን ዘመን ፈንታ፥ ክፉም ባየንባቸው ዘመኖች ፋንታ ደስ ይለናል።
16 ባሪያዎችህንና ሥራህን እይ፥ ልጆቻቸውንም ምራ።
17 የአምላካችን የእግዚአብሔር ብርሃን በላያችን ይሁን። የእጆቻችንንም ሥራ በላያችን አቅና።

ይህን ዘገባ ከዚህ ተልዕኮ ጋር በታማኝነት በጸሎት፥ በምልጃ፥ በእግር ጉዞ ጸሎት፥ እንዲሁም ለመደገፍ በደስታ ልብ ላለፈው ለ2012 ዓ.ም ለሰጣችሁት ስጦታ፥ ከልብ የሆነ ምስጋናን በማቅረብ ላብቃ። **የከበረውን የጌታችንን ልደት** በማስታወስ የተባረከ ወቅት ይሁንላችሁ።

**የቦርድ አባላት፡**

Joan Benoit
Orval and Susan Delany
Roy and Carol Fowler
Larry Halloway
Ginger Mellin
Lyle and Ruth Admunson
Vic and Bernice Voltz
Ellen Stinson

**ስለሌላ ፍሬአማ ዓመት እጅግ እናመሰግናለን!**

**ከልብ በኢየሱስ**

Henry, Judithና **መላው የቦርድ አባላት**

(**ሰብሳቢ**) Chairman - Don Van Houdenos
(**ፕሬዚዳንት**) President - **Henry Gruver**
(**ምክትል ፕሬዚዳነት**) Vice President —Henry Gruver Jr.
(**የገንዘብ ኃለፊ**) Secretary Treasurer —Heather Gruver

**ያሑዋሕ** יהוה (𐤉𐤄𐤅𐤄) (𐤉𐤄𐤅𐤄) : በዕብራይስጥ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የእሥራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ የኤልሻዳይ ስም ነው። ይህንም እጅግ እጅግ እጅግ የከበረ ፍጹም ቅዱስ ስም ጌታችንና አዳኛችን የያሑዋሕ ልጅና ቃል የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ መንፈሱ ለሚያፈቅሩት ልጆቹ አስታወቀው። יהוה

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com